የምዝገባ ጥያቄያችን በቦርዱ ውሳኔ ያልተሰጠበት መሆኑን አመልክቶ ነበር፡፡

1.3. ይሁን እንጂ በቅንጅት ስም እውቅና ተሰጥቶን ተወዳድረናል፡፡ የእጩነት መታወቂያ ቅጽ 06 ከዚያም በምርጫው ውድድር ላሸነፍን አባላት ደግሞ ቅጽ 09 ተሰጥቶናል፡፡ (ማስረጃው ተያይዟል)

1.4. እንዲሁም ቅንጅት እንደ ድርጅት ተከሶ አመራሩና አባላቱ በይቅርታ ሲለቀቁ ድርጅቱ የሚቀጥል መሆኑ፣ የተዘጉ ጽ/ቤቶችም ሁሉ እንደሚከፈቱ እና ተቋርጦ የነበረው ከገዥው ፓርቲ ጋር ተጀምሮ የነበረው ውይይት ሁሉ የሚቀጥል መሆኑ በአደራዳሪ ሽማግሌዎች ተገልጾልናል፡፡ (ማስረጃው ተያይዟል)

1.5. በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 46/86 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 25 (2) መሠረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለምዝገባ ጥያቄውን ለቦርዱ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የሚኖሩት የፓርቲው መታወቂያ ስም እና አርማ እንደተጠበቀ መቆየት ያለባቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

1.6. ተጠሪ በሕግ በተጣለበት ኃላፊነት መሠረት በአመልካች የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ የጎደለም ካለ ፓርቲው እንዲያሟላ በማድረግ ለፓርቲው የሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት መስጠት ሲገባው በአመልካች የተቋቋመውን አገር አቀፍ ፓርቲ ስም እና አርማ ለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች በመስጠቱ ይህ አቤቱታ ቀርቦበታል፡፡

## 2. <u>የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ</u>

ከዚህ በላይ በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች አመልካች የተቋቋመውን አገር አቀፍ ፓርቲ ስምና አርማ ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው አመልክቶ ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች በፓርቲው ስምና አርማ እንዲመዘገቡ ያደረገው ከሕግ ውጭ ስለሆነ ተጠሪው ቀርቦ እንዲጠየቅና ጥቅምት 18 ቀን 1998 ዓ.ም በቀረበለት ጥያቄ መሠረት በአራቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደት ለተቋቋመው አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ስምና አርማ በመመለስ የሕጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ እንዲወሰንልን እናመለክታለን፡፡

በዚህ አቤቱታ የተገለፀው ፍሬ ነገር እውነት ለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 92 መሠረት አረጋግጣለሁ፡፡

አመልካች

[signature]

አባይነህ ብርሃኑ